ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
ATTORNEY GENERAL

# የወንጀል ምርመራ እና የክስ መዝገብ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 4/2012

# የወንጀል ምርመራ እና የክስ መዝገብ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 4/2012

የኢ.ፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 943/08 በመቋቋሙና ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያየ ተቋም የነበረውን የወንጀል ምርመራ መዝገብ የማቋረጥና የመዝጋት እንዲሁም የክስ መዝገብ የማንሳትና የማንቀሳቀስ አሰራር ከአዲሱ ተቋም ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በ2003 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲ የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚቋረጥበትንና የሚዘጋበትን እንዲሁምየክስ መዝገብ የሚነሳበትን ስርአት ጠቅላላ መርሆዎች የሚያስቀምጥ በመሆኑና ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚቋረጥበትና የሚዘጋበት፣ ክስ የሚነሳበት ሥርዓት ወጥ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ለማስቻል፣ እንዲሁም ሂደቱ ከብልሹ አሰራር የፀዳ ለማድረግ እና በቂ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኢ.ፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 21(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የወንጀል ምርመራ እና የክስ መዝገብ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 4/2012” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. **“ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ”** ማለት በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
2. **“ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ”** ማለት የህግ ማስፈጸም ዘርፍ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

3. “**ዐቃቤ ሕግ**” ማለትበፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
4. “**የምርመራ መዝገብ**”ማለት በፖሊስና በዐቃቤ ሕግ በምርመራ ላይ ያለ እና ዐቃቤ ሕግ የማቋረጥ፣ የመዝጋት ወይም የመክሰስ ውሳኔ ያልሰጠበት መዝገብ ነው፡፡
5. “**የምርመራ መዝገብ ማቋረጥ**” ማለት በምርመራ ሂደት ላይ ያለን መዝገብ ሂደቱ እንዳይቀጥል ማድረግ ነው፡፡
6. “**የምርመራ መዝገብ መዝጋት**” ማለት ምርመራው የተጠናቀቀ መዝገብ ላይ በዐቃቤ ሕግ የሚሰጥ የአያስከስስም ውሳኔ ነው፡፡
7. “**የክስ መዝገብ**” ማለት ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ የመሰረተበት ማንኛውም መዝገብ ነው፡፡
8. "**ክስ ማንሳት**" ማለት ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ መስርቶበት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ እንዳይቀጥል ማቋረጥ ነው፡፡
9. “**የሕዝብ ጥቅም**”ማለትበፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤሕግ የዐቃብያነ ሕግ የአሰራር ማኑዋል እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በተመለከተው አግባብ ይሆናል፡፡
10. “**ጽሕፈት ቤት**” ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ምድብ ጽሕፈት ቤት ወይም በክልል የሚገኝ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡
11. “**ኃላፊ**” ማለት የምድብ ጽሕፈት ቤት ወይም የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ ነው፡፡
12. “**ዳይሬክቶሬት**”ማለት በሕግ ማስፈፀም ዘርፍ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ስር የተደራጀና የወንጀል ምርመራና ክስ ላይ የሚሰራ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡
13. "**ዳይሬክተር**" ማለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 12ላይ ለተመለከተው ዳይሬክቶሬት የተመደበ ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዳይሬክተር ነው፡፡
14. “**የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት**” ማለት የሕግ ጉዳዮች ኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ ቅሬታ ማስተናገጃና ሥነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

15. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የፌዴራል ወንጀል ምርመራ መዝገብን ምርመራ ማቋረጥ፣ መዝጋት፣ የክስ መዝገብን ማንሳት ውሳኔ በሚሰጥባቸው መዝገቦች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የወንጀል ምርመራ መዝገብ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የወንጀል ምርመራ መዝገብን ስለማቋረጥና ስለማንቀሳቀስ

## 4. የወንጀል ምርመራ መዝገብን ስለ ማቋረጥ

1. የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚቋረጠው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ከሆነ፣ ምርመራውን ማቋረጥ የሚችለው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ብቻ ነው፤
2. የተጀመረ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ድርጊቱ በወንጀል የማያስጠይቅ ሆኖ በተገኘ ጊዜ እንደአግባብነቱ ዐቃቤ ሕግ፣ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር ምርመራውን ሊያቋርጥ ይችላል፤
3. የወንጀል ምርመራ መዝገብ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት መዝገብ በሚቋረጥበት ጊዜ ፖሊስ አስተያየቱን በፅሁፍ እንዲሰጥ ሊጠየቅ ይችላል፤
4. ምርመራው እንዲቋረጥ የሚሰጠው ትዕዛዝ በጽሑፍ ሆኖ ምርመራው የሚቋረጥበትን ምክንያት በዝርዝር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

## 5. የተቋረጠ መዝገብን ስለማንቀሳቀስ

1.የተቋረጠ የምርመራ መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ የሚችለው መዝገቡንለማቋረጥ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የቀረ ወይም የተለወጠ ከሆነ ነው፡፡

2.የተቋረጠ የምርመራ መዝገብ እንደገና ማንቀሳቀስ የሚችለው፡-

ሀ/ምርመራው የተቋረጠው በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ከሆነ በእርሱ ወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ትእዛዝ፣

ለ/ምርመራው የተቋረጠው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ትእዛዝ ከሆነ በእርሱ ትእዛዝ፤

ሐ/ምርመራው የተቋረጠው በዐቃቤ ሕግ ከሆነ በዳይሬክተሩ ወይም በኃላፊው፤ምርመራው የተቋረጠው በኃላፊ ከሆነ በዳይሬክተር፣ ምርመራው የተቋረጠው በዳይሬክተር ከሆነ በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤሕግ ወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ብቻ ሆኖ በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የወንጀል ምርመራ መዝገብን ስለ መዝጋት

### 6. የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚዘጋበት ምክንያቶች

የወንጀል ምርመራ መዝገብ የሚዘጋው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግና በሌሎች ልዩ የስነ-ስርዓት ሕጎች በተገለፁት ምክንያቶች ነው፡፡

### 7. የምርመራ መዝገብ ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ

1. የምርመራ መዝገብ ላይ የመዝጋት ውሳኔ መስጠት የሚችለው ምርመራውን የመራው ዐቃቤ ሕግ፣ እርሱን ተክቶ የመረመረው ወይም መዝገቡ የተመራለት ዐቃቤ ሕግ ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1መሠረት ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት፡-

   ሀ/ የምርመራ መዝገቡ ለውሳኔ ከመቅረቡ በፊት ምርመራው የተጠናቀቀ ስለመሆኑ፣

   ለ/ የምርመራ መዝገቡን ለመዝጋት ምክንያት የሆነው ፍሬ ነገር ለማሟላት ተገቢና ምክንያታዊ ጥረት ስለመደረጉ፤

   ሐ/ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የተፈፀመ ወንጀል ከሆነ ምርመራው በልዩ ትኩረትመከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 8. የምርመራ መዝገብ የመዝጋት ውሳኔ ይዘት

ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ላይ የመዝጋት ውሳኔ ሲወስን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ እና በሌሎች ልዩ የስነ-ስርዓት ሕጎች የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔው የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

1. ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣የፖሊስ ምርመራ መዝገብ ቁጥር፣ የዐቃቤ ሕግ መዝገብ ቁጥር፤
2. ምርመራውን ያከናወነው የፖሊስ ተቋም ስም፤
3. የተጠርጣሪውን ስም(ያልታወቀም ከሆነ ይህንኑ በመግለጽ) ፤
4. የተጠረጠረበትን የወንጀል ዓይነት፤
5. የወንጀል ተጎጅውን /የአቤቱታ አቅራቢውን ስም/፤
6. ተፈፀመ በተባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰ ጉዳት፤
7. የተጠርጣሪው ቃል፤
8. የማስረጃዎች ዓይነትና ይዘት፤
9. ማስረጃዎችንና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት በማድረግ ዐቃቤ ሕግ የውሳኔውን ምክንያት በግልጽ በመተንተን የሰጠውን ውሳኔ፤
10. ውሳኔውን የሰጠው ዐቃቤ ሕግ ስምና ፊርማ፤
11. ውሳኔውን የሰጠው ጽሕፈት ቤት ወይም ዳይሬክቶሬት ማሕተም፤
12. ኤግዚቢት ላይ የተሰጠ ውሳኔ፤
13. የውሳኔ ግልባጭ የሚደረግላቸውን አካላት ዝርዝር፡፡

## 9. የወንጀል ምርመራ መዝገብ ከተቋረጠ ወይም ከተዘጋ በኋላ መከተል ስለሚገባው ሥነሥርዐት

1. በዚህሕግ አንቀጽ 15መሠረት ውሳኔው የደረሰው ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር በውሳኔው ካልተስማማ መዝገቡን መርምሮ ዝርዝር ምክንያት በማስቀመጥ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ለቡድን ውይይት ሊመራው ይችላል፤ የውይይቱን ቃለ ጉባዔ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ያደርጋል፤

2. በቡድን ውይይቱ የተገኘው ድምዳሜ ዐቃቤ ሕጉ ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ከሆነ ወይም ትንታኔው በቂ ካልሆነ የዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ ይሻርና በቡድን ውይይቱ ላይ በተደረሰው ድምዳሜ መሰረት መዝገቡ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. የውሳኔው ዋና ቅጂ ምርመራውን ላከናወነው የፖሊስ ተቋም ይላካል፡፡
4. የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ ውሳኔው እንዲሰጠው በአካል ቀርቦ የጠየቀ እንደሆነ የውሳኔ ግልባጭ ይሰጠዋል፡፡
5. አከራካሪ፣አሳሳቢ ወይም የሕዝብ ጥቅም ያለበት የወንጀል ጉዳይላይ የተጣራ መዝገብ ላይ ኤግዚቢት እንዲለቀቅ በዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ውሳኔበየደረጃው ያለ የበላይ ኃላፊ አውቆት እንዲለቀቅ ካላፀደቀው በስተቀር ወዲያውኑ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ሆኖምበየደረጃው ያለ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔውን በአስር ቀናት ውስጥ ካላሳወቀ የዐቃቤሕግ ውሳኔ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የውሳኔው ግልባጭ በዚህ ሕግ አንቀጽ 15ላይ ለተዘረዘሩት ይላካል፡፡

10. ***<u>በተዘጋ መዝገብ ላይ የጽሕፈት ቤትና የዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>***

በተዘጉ መዛግብት ላይ ጽሕፈት ቤት ወይም ዳይሬክቶሬቱ እንደአግባብነታቸው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

1. ***<u>ጽሕፈት ቤት</u>*** ፡-

ሀ/ በጽሕፈት ቤቱ የተሰጠን ውሳኔ አደራጅቶ የመያዝ፤

ለ/የተሰጠው ውሳኔ ሕግን ተከትሎ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ/በመዝገብ ላይ በስነ-ምግባር ጉዳለት ምክንያት ተጠያቂ መሆን ያለበት ዐቃቤ ሕግ ካለ ለዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የማቅረብ ፡፡

2. <u>ዳይሬክቶሬት፡-</u>

ሀ/ ከጽሕፈት ቤት የተሰጠን ውሳኔ ወይም ግልባጭ የተደረገለትን እንዲሁም በዳይሬክቶሬቱየምርመራ መዝገብ ላይ የተሰጠን ውሳኔ አደራጅቶ የመያዝ፤

ለ/በዳይሬክቶሬቱ ዐቃብያነሕግ እና ከጽሕፈት ቤት ግልባጭ የተደረገለትን ውሳኔ ሕግን ተከትሎ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ/በዳይሬክቶሬቱ መዝገብ በስነ-ምግባር ጉዳለት ምክንያት ተጠያቂ መሆን ያለበት ዐቃቤ ሕግ ካለ ለዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የማቅረብ፣ ከጽሕፈት ቤት በመጣ መዝገብ ላይ በስነ-ምግባር ጉድለት ተጠያቂ መሆን ያለበት ዐቃቤ ሕግ ካለ ለዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ እንዲቀርብ ለፅሀፈት ቤቱ ማሳሰቢያ በመስጠት መመለስ፡፡

3. <u>የጽሕፈትቤት እና የዳይሬክቶሬት የወል ሥልጣንና ኃላፊነት፡-</u>

ሀ/የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የለውም ብሎ ካመነ የወንጀል ምርመራ መዝገቡን አስቀርቦ የመመርመር፣ ትንታኔ ወይም ማብራሪያ መጠየቅ፣ እንዲሁም የተዘጋው መዝገብ ላይ ተጨማሪ ምርመራ እንዲካሄድ አቅጣጫ መስጠት፣ የተሰጠውን ውሳኔ የሚያስቀይር ነገር ካለ የመቀየር፤

ለ/ የተዘጉ መዝገቦች ላይ መስተካከል ያለባቸውን ችግሮች በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ የማመላከት፣ ለበላይ አመራሩ ሪፖርት የማቅረብ፤

ሐ/በሪፖርት ወይም በአቤቱታ የተገኙ ድክመቶች እንዲስተካከሉ የማድረግ ኃላፊነቶች አለባቸው፡፡

11. <u>በተዘጋ መዝገብ ላይ የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ላይ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. ከጽሕፈት ቤቶችና ከዳይሬክቶሬቶች ግልባጭ የተደረጉለትን ውሳኔዎች አደራጅቶ መያዝ፤
2. ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ የሰጠባቸው መዝገቦች በሙሉ ግልባጭ የተደረጉለት መሆኑን ማረጋገጫ መጠየቅ፤ በአካልና በማንኛውም መንገድ ማጣራት፤
3. የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን በሚካሄድበት ጊዜ የተገኙ የአሰራር ክፍተቶች ወይም ድክመቶች እንዲስተካከሉ፤ በግል ተጠያቂ መሆን ያለባቸውን አግባብ ባለው መንገድ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ፤
4. የሕግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን በሚያደርግበት ጊዜ ዐቃቤ ሕግ የሰጠው ውሳኔ አሳማኝ ባልሆነ ጊዜ መዝገቡን አስመጥቶ በመመርመር በመዝገቡ ላይ የተሰጠው ውሳኔን ሊያስቀይር የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲያገኝ ይህንኑ በበቂ ትንታኔ በማስደገፍ ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የውሳኔ ሐሳቡን የማቅረብ፤
5. ከምድብ ጽሕፈት ቤት በመጣ መዝገብ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት በግልባጭ ለዳይሬክቶሬቶች የማሳወቅ፡፡
6. የተዘጉ ወይም የተቋረጡ መዝገቦችን ኦዲት በሚያደርግበት ጊዜ የሚገኙ ክፍተቶችን መነሻ በማድረግ ለቀጣይ ማስተማሪያነት ወይም ማስልጠኛነት የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም የውሳኔ አሰጣጣቸው አስተማሪ የሚሆኑ ውሳኔዎች በተቋሙ በሚታተሙ የህትመት ውጤቶች እንዲታተሙ ሁኔታዎችን የማመቻቸት

## ክፍል ሦስት

## የክስ መዝገብ ስለማንሳት እና ስለማንቀሳቀስ

### 12. የክስ መዝገብ ስለሚነሳባቸው ምክንያቶች

1. ማንኛውምየክስ መዝገብ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ሊነሳ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ክስ የሚነሳው፡-

   ሀ/ የተከሳሽ ማንነት ላይ ስህተት ሲያጋጥም፤

   ለ/ የሕዝብ ጥቅምን ለማስከበር ሲባል፤ እና

   ሐ/ በሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ነው፡፡

13. <u>የክስ መዝገብ ስለማንሳት</u>

1. የቀረበው ክስ የሕዝብ ጥቅምን የማያስከብር መሆኑ ሲታመንበት ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 12/2/ሀ/ መሰረት በስህተት ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም ሌሎች ክስ የሚነሳባቸው ምክንያቶች ሲያጋጥሙ ዐቃቤ ሕግ ከኃላፊው ወይም ከዳይሬክተሩ ጋር በመነጋገር ኃላፊው ወይም ዳይሬክተሩ ሲያምንበት ክሱን ሊያነሳ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን የተሰጠ ከሆነ፣ ክስ የሚቋረጠው በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤሕግ ወይም በጠቅላይ ዐቃቤሕግ ትዕዛዝ ብቻ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተመለከተው ቢኖርም በቀረበው ክስ ላይ የተጠቀሰው ወንጀል አለመፈጸሙ፣ በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ክስ መሆኑ ወይም በተከሳሹ ማንነት ላይ ስህተት የተሰራ መሆኑ በማይስተባበል መልኩ የታወቀ በሆነ ጊዜ ክሱን የምድብ ጽ/ቤት ሀላፊው ወይም ዳይሬክተሩ ሊያቋርጡት ይችላሉ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም የሙስና ወንጀሎች፣ የታክስና የጉምሩክ ወንጀሎች፣ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎች፣በሴቶችናሕፃናት ላይ የሚፈጸሙወንጀሎች፣አደንዛዥ እፅ ማዘዋወር ወንጀሎችእንዲሁም የሽብርተኝነት ወንጀሎች ላይ የተመሰረቱ፡ ክሶች የሚነሱት በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ብቻ ነው፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 3 እና 5 ላይ በተመለከተው መሰረት ክስ ሊነሳ ይገባል ብሎ የሚያምን ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር ሀሳቡን በዝርዝር ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በጽሑፍ በማቅረብ እንዲወሰን ማድረግ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 እና4 በተመለከተው መሰረት ክሱ ሊነሳ ይገባል ብሎ የሚያምን ዐቃቤ ሕግ በስነ ስርዓት ሕጉ መሰረት ተገቢውን ቀጠሮ በመጠየቅ ከኃላፊው ወይም ከዳይሬክተሩ ጋር ሊነጋገር ይችላል፡፡

8. በዚህ መመሪያ መሰረት የክስ ማንሳት ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ በጽሑፍ ሆኖ በበቂ ትንታኔ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡
9. በዚህ አንቀጽ መሰረት በምድብ ጽ/ቤት ሀላፊዎች፣ ዳይሬክቶሬቶች፣ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ክሶች በሚነሱበት ወቅት በተቻለ አቅም ጉዳዩን በመከታተል ላይ የሚገኘው ዐቃቤ ሕግ አስቀድሞ እንዲያውቀውና አስተያየቱን በፅሁፍ እንዲሰጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡
10. በዚህ መመሪያ መሰረት በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ወይም በሀላፊ የሚነሳ ክስን በተመለከተ ዐቃብያነ ህግ የማስፈጸም ሀላፊነት አለባቸው

14. <u>የተነሳ የክስ መዝገብን ስለማንቀሳቀስ</u>

የተነሳ የክስ መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ የሚችለው፡-

1. ክሱን ያነሳው አካል በሚሰጠው ዝርዝር ትንታኔን በያዘ ትእዛዝ፤
2. ክሱ የተነሳበት ምክንያት በየደረጃው ባለ ኃላፊ ተመርምሮ ትክክል አለመሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም
3. ክሱ የተነሳበት ምክንያት ጊዜያዊ ሆኖ መዝገቡን ለማንሳት የተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ሲኖርና መሟላቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡

15. <u>ግልባጭ ስለማድረግ</u>

1. ማንኛውም የምርመራ እና የክስ መዝገብ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ለህግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ግልባጭ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ/ ጽሕፈት ቤት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ለኃላፊው እና የወንጀል ጉዳዩ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት፤

ለ/ ዳይሬክቶሬት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ለዳይሬክተሩ እና ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤

ሐ/በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ለጠቅላይ ዐቃቤሕግ ግልባጭ መደረግ አለበት፡፡

3. ክስ ማንሳትን በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ክሱን እየተከታተለ ላለው ምድብ ጽሕፈት ቤት ወይም ዳይሬክቶሬት እና ምርመራውን ላከነወነው የፖሊስ ተቋም ግልባጭ መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ አቤቱታ

### 16. በመዝገብ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ በጠቅላላ

1. ማንኛውም በምርመራ መዝገብ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ቅሬታ በየትኛውም የስራ ክፍል በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. አቤቱታው ወይም ቅሬታው የቀረበለት የስራ ክፍል ኃላፊ መዝገቡን የሚከታተለው ጽሕፈት ቤት ከሆነ ከጽሕፈት ቤቱ ጀምሮ ወይም መዝገቡን የሚከታተለው ዳይሬክቶሬት ከሆነ ከዳይሬክቶሬቱ ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ድረስ ተዋረዱን ጠብቆ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1እና2 ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዐቃብያነሕጎችን የስነምግባር ጉዳይን የሚመለከት ከሆነ ለሕግ ጉዳዮች ኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ ቅሬታ ማስተናገጃና ሥነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ሊቀርብ ይችላል፡፡

### 17. አቤቱታ ስለማቅረብ

በምርመራ መዝገብ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ፡-

1. የወንጀል ተጎጂ/የግል ተበዳይ/ ወይም ሕጋዊ ወኪል፣
2. የወንጀል ተጎጂ ቤተሰብ፣
3. ፖሊስ፣
4. ተከሳሽ ወይም ጠበቃ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ፣
5. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው የተነካ ሰዎች፣
6. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም ሰው፣
7. ቅሬታው ከስነምግባር ጋር የተገናኘ ከሆነ ማንኛውም ሰውቅሬታዎችን በጽሑፍ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

18. <u>የምርመራ መዝገብ መቋረጥ አቤቱታን ስለመስማት</u>

1. በተቋረጠ የምርመራ መዝገብ ላይ ቅሬታ ያለው አካል፣ አቤቱታውን፣

ሀ/የምርመራ መዝገብ የተቋረጠው ጽሕፈት ቤት ባለ ዐቃቤ ሕግ ከሆነ ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፣ ዳይሬክቶሬት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ ከሆነ ለዳይሬክተሩ፣

ለ/የምርመራ መዝገቡ የተቋረጠው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ከሆነለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. አቤቱታው በዚህ ሕግ አንቀጽ 20(3) መሰረት ይመረመራል፡፡

3. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡

19. <u>የምርመራ መዝገብ መዘጋት ላይ አቤቱታን ስለመስማት</u>

1.በተዘጋ የምርመራ መዝገብ ላይ ቅሬታ ያለው አካል፤ አቤቱታውን፣

ሀ/የምርመራ መዝገብ የተዘጋው ጽሕፈት ቤት ባለ ዐቃቤ ሕግ ከሆነ ለኃላፊ፣

ለ/ዳይሬክቶሬት ላይ ባለ ዐቃቤ ሕግ ከሆነ ለዳይሬክተሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

2.አቤቱታ ቀርቦ በኃላፊ ወይም በዳይሬክተር በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘአካል ቅሬታውን እንደአስፈላጊነቱ እስከ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ድረስ ማቅረብ ይችላል፡፡

3. አቤቱታው በዚህ ሕግ አንቀጽ 20መሰረት ይመረመራል፡፡

4. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡

20. <u>አቤቱታ ስለሚመረመርበት አግባብ</u>

1. ለጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሚቀርብ ቅሬታ በኃላፊው የሚወሰን ሆኖ ውሳኔውን ከሰጠው ዐቃቤ ሕግ ጋር በመነጋገር እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱና እንደመዝገቡ ሁኔታ የዐቃቤያነ ሕግ ቡድን በማቋቋም እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ለዳይሬክቶሬትየሚቀርብ ቅሬታበዳይሬክተሩ የሚወሰን ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ባለው አስተባባሪ የሚመራ የዐቃቢያነ ሕግ

ቡድን በማቋቋም የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡለት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ቡድኑ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና መዛግብትን ደብዳቤ በመጻፍ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡

3. ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ አቤቱታ በራሱ የሚወሰን ሆኖ በአማካሪዎች ወይም እንደአስፈላጊነቱ በሚቋቋም ቡድን ሊመረመር ይችላል፡፡
4. ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚቀርብ አቤቱታ፡-

   ሀ/ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚወሰን ሆኖእንደአስፈላጊነቱ በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤሕጉ ወይምበአማካሪዎች ወይም ሊመረመር ይችላል፡፡

   ለ/ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡

## 21. አቤቱታ የሚሰማ አካል ተግባርና ኃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሠረት አቤቱታን እንዲያስተናግድ የተገለጸ አካል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. የሚቀርብላቸውን አቤቱታ መዝግቦ የመያዝ፤
2. የቀረበውን አቤቱታ በዜጎች ቻርተር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት በጽሑፍ መልስ መስጠት፡፡
3. የቀረበውን አቤቱታ ያልተቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለጉዳዩ የማስረዳትና በጽሑፍ መልስ በመስጠት ባለጉዳዩ በተሰጠው ዉሳኔ ላይ ካልተስማማ በቀጣይ አቤቱታውን ማቅረብ የሚችልበትን አካል የመግለጽ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 22. የክስ መዝገብ መነሳትን በተመለከተ ስለሚቀርብ አቤቱታ

በዚህ ክፍል የምርመራ መዝገብ መቋረጥና መዘጋትን አስመልክቶ አቤቱታ የሚቀርብበትና የሚመረመርበት ስነ-ስርዓትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ክስ ማንሳትን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

23. **የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች**

   1. በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የወንጀል ምርመራን ማቋረጥ፣ የምርመራ መዛግብትን መዝጋት እና ክስ መቋረጥ በሚመለከት በመጋቢት 12/2006 ዓ.ም በፍትሕ ሚኒስቴር የወጣው የአሰራር ስርዓት መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
   2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

24. **የሥነ ምግባር ተጠያቂነት**

   የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መተላለፍ ወይም በመመሪያው መሠረት ተግባራትን አለማከናወን በዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ደንብ መሰረት የዲስፕሊን ቅጣት ያስከትላል፡፡

25. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም**